"ኦርቶዶክስ ሐገር ናት"

የማንነት እና የሉዓላዊነት ምሰሶ

"ኦርቶዶክስ ሐገር ናት" የሚለው አባባል ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፖለቲካዊ መፈክር ብቻ ሳይሆን፣ በደም እና በታሪክ የተጻፈ ሕያው እውነት ነው። ቤተክርስቲያኗ የሀገሪቱ የጀርባ አጥንት ብቻ ሳትሆን፣ ኢትዮጵያዊነት (The Ethiopian Psyche) የተሰኘውን ስነ-ልቦና ቀርጻ የሰራችው እሷ ናት። የራሳችንን ፊደል ጠብቃ በማቆየት የጽሕፈት እና የንባብ ባህልን ያወረሰች፣ የራሳችንን የዘመን አቆጣጠር (Calendar) የቀመረች፣ እና "ፍትሐ ነገሥት"ን ደንግጋ የህግ እና የስርዓት መሰረት የጣለች የሥልጣኔ እናት ናት። በታሪክ ፈተናዎች ወቅት፣ ኢትዮጵያ በውጭ ወራሪዎች ስትወረር፣ ታቦተ ሕጉን ተሸክማ ወደ ጦር ግንባር በመዝመት፣ ከአድዋ እስከ ማይጨው የሀገሪቱን ሉዓላዊነት እና ነጻነት ያስጠበቀችው እሷ ናት። ለ1,600 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያዊነት እና ኦርቶዶክሳዊነት ተዋህደው አንድ አካል ሆነው ኖረዋል። ህዝቡ ሲጾም፣ ሲለብስ፣ ሲያለቅስ እና ሲደሰት፣ መልክና ቅርጽ የሰጠችው ቤተክርስቲያኗ ናት። በዚህ ረገድ፣ ቤተክርስቲያኗ የኢትዮጵያ "ባህል" እና "ነፍስ" መሆኗ አጠያያቂ አይደለም ፤ አሁን ላይ ያለው ኢትዮጵያዊ ባሕል በከፍተኛ ሁኔታ በቤተክርስቲያኒቱ influence የተደረገ ነው ፤ ቤተክርስቲያኒቱ ያል ገባችበት ባሕላዊ ሁነት የለም።

እንዲሁም ቤተክርስቲያኒቱ ከአክሱም ነገሥታት ጀምሮ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆና ለ1,600 ዓመታት ቆይታለች በዚህም ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ተለይታ መንግሥታዊ ድጋፍ ነበራት ስለዚህም ኦርቶዶክስ መሆን ማለት የኢትዮጵያዊነት "default state" ሆኖ ቆይቷል ማኅበረሰቡም by default ኦርቶዶክሳዊ ባሕልን የሚያንጸባርቅ ሆኖ ነበር።

ከ"ማህበረሰብ ማዕከልነት" ወደ "አገልግሎት ሰጪነት" የተደረገ ሽግግር ይህ "ባህል እና መንግስት የመሆን" ታላቅ ታሪክ ግን በውስጡ አንድ ስውር እና አደገኛ የሆነ የመዘናጋት ወጥመድ ይዞ መጣ። ቤተክርስቲያኗ ለዘመናት የሁሉም ነገር "ማዕከል" እና የባህሉ አካል ስለነበረች፣ አሰራሯ ቀስ በቀስ ወደ "ተቋማዊ አገልግሎት ሰጪነት" (Institutional Service Provider) ተቀየረ። ድሮ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሰፈሩ "ልብ" ነበረች፤ ዛሬ ግን እንደ "ወሳኝ ኩነት ጽ/ቤት" ወይም እንደ አንድ የመንግስት ቢሮ ሆናለች። ቤተክርስቲያን መሳተፊ የአንድ አማኝ መንፈሳዊ ግኑኝነት የሚያደርግበት ቦታ ሳይሆን ባሕላዊ ግዴታን የሚፈጽምበት ቦታ ሆነች ምእመኑ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጣው ልክ እንደ ቀበሌ ጽ/ቤት "ጉዳይ" ሲኖረው ብቻ ሆነ። ልጅ ሲወለድ ለክርስትና፣ ሲታመም ለፀበል፣ ሲሞት ለፍትሐት፣ ወይም ሲያገባ ለተክሊል ይመጣል (ይህም አሁን ላይ ጠፍቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያገባ ጥቂት ሆኗል)። ጉዳዩን ይፈጽማል፤ ክፍያውን ይከፍላል፤ ይመለሳል። ቤተክርስቲያኗ የምእመናን "መኖሪያ ቤት" መሆኗ ቀርቶ፣ አልፎ አልፎ ጎራ የሚባልባት "ጉዳይ ማስፈጸሚያ" ሆናለች። ተወልዶ ለክርስትና መጥቶ አንድ አንድ ንግሦችን እና እንደ ጥምቀት እና መስቀል የመሰሉ አደባባይ በዓላትን ለማክበር ካልሆነ በስተቀር ቤተክርስቲያን የማይመጣ ነገር ግን ባሕላዊ ክርስቲያን ሆኖ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚቀጥል ማኅበረሰብ ተፈጥሯል ፤ አኗኗሩ እምላክ የለሽ ቢሆንም ኦርቶዶክሳዊነት ከኢትዮጵያዊ ባሕል ጋር ከመቆራኘቱ የተነሣ "የእምላክ የለሽ" ኑሮው ያልታየው ሕዝብም ተቋቁሟል። በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኒቱ ልክ እንደ አንድ ማኅበራዊ ስብስብ ተቆጠረች (እንደ እድር ያሉ ማሕበራት አይነት)።

አሁን ግን ዘመኑ እየተለወጠ ነው ቤተክርስቲያኒቱ በቀድሞ ጊዜ የነበራት የበላይነት የለም ፤ ብሔራዊ ሃይማኖት የመሆኗን ነገር አጥታለች። የባሕል የበላይነትም ቢሆን በሉላዊነት (globalization) ምክንያት በምዕራባዊ ባሕል እየተሸረሸረ ነው ፤ ወጣቱ በሴኩላሪዝም አማካኝነት ዓለማዊ እየሆነ እንደ ቀድሞው

“ክርስቲያናዊው ባሕል” መከተል የግድ እንዳልሆነ እያየ ነው። ቤተክርስቲያን ግን አሁንም አሠራሯ “የመንግሥታዊ ሃይማኖት mindset” እንደያዘ ነው። ወጣቱ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እምነቱን የሚሸረሽሩ ጥቃት እየመጣበት ነው ቤተክርስቲያኒቱም የሃይማኖቱን ክልል በብቸኝነት የተቆጣጠረችበት ጊዜ አይደለም አሁን ፤ ሰዉ ከኦርቶዶክሳዊነት ሌላም ምርጫ ሃይማኖቶች እንዳሉ እያየ ነው ብዙ ምዕመናችንም እየተወሰደ ነው በዚህ ረገድ እንደ ጴንጤው ማኅበረሰብ የተሳካለት የለም።

ግንባር አንድ፡ የ"ወራሪ" ማወንገል **(Aggressive Evangelism)**

የጴንጤው ማኅበረሰብ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የነበራትን የህገራዊውም ሆነ የባሕላዊ የበላይነት አልነበራቸውም ፤ Minority movement ሆነው ነው የተነሡት ስለዚህም ህልውናቸውን ለማስጠበቅ የነበራቸው ብቸኛ መንገድ ማወንገል ነበር። ለእነርሱ ማወንገል የህልውናቸው መሠረት ነበር ፤ ኦርቶዶክስ ማወንገልን ባትሠራም default state በመሆኗ እንዲሁም ቁጥሯ ይጨምራል እነርሱ ደግሞ ገና minority በመሆናቸው ራሳቸውን establish ማድረግ ነበረባቸው ስለዚህም ማወንገልን የሞት ሽረት እንቅስቃሴ አድርገው ተያያዙት ለ1600 ዓመታት ወንግሎ የነበረውን ማኅበረሰብ “ጌታን ተቀበል” በሚል ስብከት በትልቅ ቅንዓት (zeal) ተነሡ።

እኛን እየቀደሙን ያለው በመጀመሪያው ግንባር **"በማጥቃት" (Going Out)** ነው። እነሱ ቤተክርስቲያንን እንደ ህንጻ ሳይሆን እንደ እንቅስቃሴ (Movement) ነው የሚያዩት። የእነሱ ስልት ሰው ወደ አዳራሽ እስኪመጣ መጠበቅ ሳይሆን፣ ሰው ወዳለበት መሄድ ነው። በታክሲ ውስጥ፣ በአውቶቡስ፣ በየመንገዱ፣ በየቤቱ እያንኳኩ "ወራሪ ስብከት" ያካሂዳሉ። አዎ፣ የመንገድ ላይ ጩኸታቸው ሊረብሽን ይችላል፤ "ስነ-ስርዓት የላቸውም" ብለን እንተቻቸዋለን። ነገር ግን እነሱ "ሰውን ለማዳን ስነ-ስርዓት ምን ይሰራል?" በሚል የህልውና መንፈስ ቆርጠው ወጥተዋል። እኛ "የተከበረችውን ቤተክርስቲያን እንዴት መንገድ ላይ እናውላለን?" በሚል ጨዋነት ውስጥ ሆነን፣ በወርቅ የተለበጠ ካቴድራል ውስጥ ሰው እስኪመጣ እንጠብቃለን። እነሱ ግን አቧራው ውስጥ፣ ሰው ያለበት ቦታ ድረስ ወርደው፣ እያነጋገሩ፣ እየጠየቁ ይወስዱብናል።

ግንባር ሁለት፡ የ**"ማህበረሰብ"** እና የጓደኝነት ወጥመድ **(Community Formation)** ወንጌላውያኑ የሚያሸንፉት በመንገድ ላይ በመጮህ ብቻ አይደለም፤ ትልቁ ድላቸው ሰውየውን ካገኙ በኋላ በሚፈጥሩት **"ማህበረሰብ" (Community)** ነው። ይህ ሁለተኛው እና ወሳኙ ግንባር ነው። ወንጌላውያኑ ጋር አንድ ሰው ሲሄድ፣ የሚያገኘው ስብከት ብቻ አይደለም፤ "ጓደኛ" ያገኛል፣ "ቤተሰብ" ያገኛል። ሙሉ ሳምንት የሚሰራ ፕሮግራም አላቸው። ሰውየው ብቸኝነት አይሰማውም። አዲስ ሰው ሲመጣ ብቻውን እንዲቀመጥ አይተዉትም፤ ያስተዋውቁታል፣ በቡድን (Cell group) ያቅፉታል፣ በሳምንቱ ደውለው ይጠይቁታል። እኛ ጋር ግን አንድ ሰው እሁድ መጥቶ ሊያስቀድስ ይችላል፣ ነገር ግን ማንም "እንዴት ነህ?" የሚለው የለም። ከቅዳሴ በኋላ ግቢው ባዶ ነው። ወጣቱ ስለ ህይወቱ፣ ስለ ትዳሩ፣ ወይም ስለ ስራው የሚማከርበት ጓደኛ አያገኝም። እነሱ "ፍቅር እና ጓደኝነት" በማቅረብ የብቸኛውን ትውልድ ልብ ሲወስዱ፣ እኛ ግን እውነት ይዘን በብቸኝነት እንዲኖሩ ፈርደንባቸዋል።

**"ኦርቶዶክስ ሐገር ናት"** እንደ ማደንዘዣ በዚህ ዘመን ያለው ትልቁ አደጋ፣ "ኦርቶዶክስ ሐገር ናት" የሚለው መፈክር እንደ "ማደንዝዣ መርፌ" ሆኖ ማገልገሉ ነው። "ሀገሩ የኛ ነው፣ ታሪኩ የኛ ነው፣ 60 ሚሊዮን ነን" እያልን በትላንት ታሪክ ስንጽናና እና ስንታለል (የእኛ ነው ዋሻው እምነቱ ጸበሉ የሚለው መዝሙር የዚህ አንድ ውጤት ነው) ወንጌላውያኑ ግን በሁለቱም ግንባር ጦርነት ከፍተዋል፡- አንደኛ፣ ወጥቶ በመፈለግ **(Evangelism)**፣ ሁለተኛ፣ አቅርቦ ጓደኛ በማድረግ **(Community)**። እኛ ቤተክርስቲያንን እንደ "ቢሮ"፣

እነሱ ደግሞ እንደ "ሕያው ቤተሰብ" እያዩት ነው። የዚህ ውጤት የሚሆነው፣ ሀገሩ፣ ፊደሉ እና ታሪኩ የኛ እንደሆነ ይቀጥል ይሆናል፤ ነገር ግን በእነዚህ ፊደላት የሚጽፈው፣ በምድሪቱ የሚራመደው እና ባህሉን የሚወርሰው ህዝብ የሌላ እየሆነ ነው።

ዛሬ አብያተ ክርስቲያናቶቻችን በንግሥ እና በጥምቀት በህዝብ ሲጥለቀለቁ ስናይ "ኦርቶዶክስ ሐገር ናት፤ ህዝቡም አለ" ብለን የምንጽናና ቢሆንም፣ ይህ እይታ አደገኛ የመዘናጋት ምንጭ ነው። እውነታው ግን ቤተክርስቲያኗ እያደገች ያለው በወሊድ (Biological Growth) እንጂ በስብከት (Conversion Growth) ባለመሆኑ፣ የህዝብ ቁጥር ሲጨምር የምእመኑ ቁጥር የጨመረ ቢመስልም ከጠቅላላው የህዝብ ቁጥር አንጻር የነበረን ድርሻ (Percentage) ግን እየቀነሰ ነው። እኛ በታሪክ ካባ ተሸፍነን ስንተኛ ወንጌላውያኑ በዘመናዊ አደረጃጀት የእኛን በጎች በመቀማት ትውልዱን እየወሰዱት በመሆኑ፣ "ኦርቶዶክስ ሐገር ናት" የሚለው እውነት እንዳለ ሆኖ፣ ሀገሩ የኛ ሲሆን ህዝቡ ግን የሌላ እንዳይሆን ከፍተኛ ስጋት አለ።

ስለዚህ፣ ክብራችን የሚጠበቀው ታሪካችንን በመተረክ ብቻ ሳይሆን፣ አባቶቻችን ኢትዮጵያን እንደሰሩ ሁሉ፣ እኛም ትውልድ በመስራት ነው። በኋላ ታሪክ መኖር አንችልም በዚህ ዘመን ኦርቶዶክሳዊነትን እንደ default state እየቆጠርን መቀጠል አንችልም ይልቅስ አዲስ ምዕመንን ለማምጣትም ሆነ ያሉትን ለመያዝ ልዩ የሆነ እንቅስቃሴ ያስፈልገናል። ለምሳሌ በአሁን ጊዜ አንድ ወጣት ኦርቶዶክስ መሆን ቢፈልግ ማንን ነው ማናገር ያለበት? ማንስ ነው ወደ ቅዳሴ ወደ ሥርዓተ አምልኮ እየወሰደ የሚያለማምደው? ከሰንበት ትምህርት ቤት ኮርስ ወጣ ብሎ ለአዲስ አማኞች ብቻ የተዘጋጀ ልዩ ኮርስስ ከየት ያገኛል? በካቶሊኩ ዘንድ OCIA የተባለ ፕሮግራም አለ ቋሚ ጊዜ ሆኖ እስከ ጥቀት አዲስ አማኞችን ሚያስተምር በእኛ ዘንድ ግን እንደዚህ አይነት መዋቅርም የለም ፤ እንኳንስ ወጥተን ሌላውን ማምጣት ላይ ማተኮር ይቅርና አንድ ሰው በራሱ ተነሣሽነት እንኳን ቢመጣ ለመቀበል ዝግጁ የሆነ አሠራር የለም።

እንዲሁም ከትምህርቱ በተጨማሪ አብያተ ክርስቲያኖቻችን socializing የመሰለ መርሐ ግብር የላትም ሰው ቅዳሴ ይመጣል ያመልካል ወደ ቤቱ ይሔዳል ፤ እንደ በፊቱ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የማኅበረሰቡ ማዕከል መሆኑን አቁሟል ይልቅስ በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሳተፉትን ሰዎች አናውቃቸውም ስለዚህ አዲስ ሰው እንኳን ቢመጣ የሚያስተውለውም የለም። ሥርዓተ አምልኮውም በጣም ከሕዝቡ የረቀቀ ነው ፤ ሥርዓተ አምልኮውን ለሕዝቡ ተደራሽ ከማድረግ ይልቅም ሥራው እየተሠራው ያለው ሥርዓተ አምልኮው ጎን ለጎን የሚገዳደር ፕሮግራም ነው።

አሁን ላይ ኦርቶዶክስ ልሁን ያለ ሰው በቀላሉ ኦርቶዶክስ መሆን አይችልም ብዙ ውጣ ውረዶች ማለፍ ስላለበት ከሁሉም የጠነከረው ብቻ ነው የሚሆነው ፤ በአንጻሩ ደግሞ ጴንጤ መሆን በጣም ቀላል ነው ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ ነው የሚጠብቀው ማወንገሉም ማኅበረሰቡም። ለዚህም ይመስላል ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ ኦርቶዶክሱ ራስን የመከላከል mindset ያዳበረው ፤ ቤተሰብ ልጁ ጴንጤ እንዳይሆን ይፈራል ፣ በጴንጤ ጓደኛም influence ተደርገው ወጣቶች እንዳይወሰዱ ይፈራል ስለዚህም ጓደኝነታቸውን ወሰን እንዲያበጁበት ይሠራል። አንድ የሥራ ቦታ ውስጥ 3 ኦርቶዶክስ እና አንድ ጴንጤ ቢኖሩ የሚፈራው ጴንጤው እንዳይወስዳቸው ነው ኦርቶዶክሱ የሚሠራው በእርሱ እንዳይወሰድ ነው እንጂ ለማምጣት አይሠራም ፤ አልታጠቀማ ደግሞም ቢታጠቅም አሁንም ቢሆን ራሱን እንደ ጠበቂ ነው እንጂ የሚያየው evangelism የክርስትና ዋና ነገር ተደርጎ አልታየም።

አሁን ግን ጊዜው ሳይረፍድ በፊት መንቃት አለብን ከእንግዲህ ወዲህ በ default state mindset መቀጠል አንችልም ከዚህ በፊት አይነኬ ብለን የምናስባቸው ቦታዎች ሳይቀሩ ባለፈው እንደ ጎንደር አይነት

እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል ስለዚህ እኛ ተኝተን መቀጠል አንችልም።  ይህን ችግር ለመቅረፍ ቤተክርስቲያን ሁለት መሰረታዊ ለውጦችን ማድረግ አለባት፡

1. መውጣት **(Evangelism):** ወንጌሉን ይዘን ወደ ህዝቡ መውረድ ስራ ቦታ እና ሰፈር ውስጥ ያለውን ህዝብ መድረስ።
2. ማቅረብ **(Community):** አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ከ"ጉዳይ ማስፈጸሚያነ" ወደ "የክርስቲያኖች መኖሪያ ቤትነት" መቀየር። ምእመኑ ጓደኛ የሚያፈራበት፣ የሚደመጥበት እና ብቸኝነት የማይሰማው ማህበረሰብ መፍጠር።
3. የአዲስ ተጠማቂዎች መዋቅር ማዘጋጀት፡ በማወንገል ማምጣት የተቻለውን ሰው ፣ ኮርስ የሚያተምር ፣ ሥርዓተ አምኮውን የሚያተምር ፣ ከአጥቢያው ምዕመናን ጋር የሚያግባባ መዋቅር ተቀርጾ ወደ ሥራ ማስገባት
4. ሥርዓተ አምልኮ፡ ሥርዓተ አምልኮውን ለሕዝቡ ተደራሽ ማድረግ ፤ ቢቻል ሕዝቡ በሚሰማው ቋንቋ ፣ እሱም ባይቻል መተርጎም ፣ ትርጉሙን ማስተማር ፣ ዋና ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ ፣ የአጥቢያው ምዕመናን በሚመቻቸው ሰአት አማክሮ ቅዳሴውን መጀመር በአጠቃላይ ሁሉንም ነገር ቅዳሴ ተኮር ማድረግ።

እነሱ በሁሉም በኩል እየሰሩ፣ እኛ በአንዱም ሳንሰራ "ኦርቶዶክስ ሐገር ናት" ማለት የህልውና ራስን ማጥፋት ነው።